የኢ.ትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ኤምባሲ
አታዋ
**EMBASSY OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**
**OTTAWA**

# የሀዘን መግለጫ

በካናዳ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ክብርት ወ/ሮ ብርቱካን አያኖ በኤምባሲው ዲፕሎማቶች እና የስራ ባልደረቦች ስም በጀግናው አትሌት ሻምበል ምሩጽ ይፍጠር ህልፈተ ህይወት የተሰማቸውን ልባዊ ሀዘን ይገልጻሉ፡፡

ሻምበል ምሩጽ ይፍጠር በረጅም ርቀት ለሀገራችን አትሌቶች ፈር ቀዳጅ የሆነ አትሌት ሲሆን በዚህ ስኬቱም በአድናቂዎቹ ዘንድ ማርሽ ቀያሪው የሚል ቅጽል ስም ጭምር ተበርክቶለት የነበረ ብርቅዬ አትሌታችን ነበር፡፡

ሻምበል ምሩጽ በኦሎምፒክ የ10 ሺህ እና በ5 ሺህ ሜትር እሩጫዎች ሁለት ጊዜ በተከታታይ አሸናፊ በመሆን ለሀገሩ የወርቅ ሜዳሊያ በማስገኘት ብሎም በተለያዩ ሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች በመሳተፍ በርካታ ሜዳሊያዎችን በመሸለም የሀገራችን ባንዲራ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ በማድረግ የብሔራዊ ኩራታችን ምንጭ ነው፡፡

ሻምበል ምሩጽ ይፍጠር ባደረበት ከፍተኛ ህመም በቶሮንቶ Bridgepoint Healthcare በህክምና ሲረዳ ቆይቶ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 22/2016 ዓ.ም ከምሽቱ 9:05 pm አካባቢ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡

በካናዳ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ በጀግናው አትሌት ሻምበል ምሩጽ ይፈጠር ህልፈተ ህይወት የተሰማውን ልባዊ ሀዘን በድጋሚ እየገለጸ፣ለቤተሰቦቹ፣ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብና ለአድናቂዎቹ በሙሉ መጽናናትን ይመኛል፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኤምባሲ

አታዋ

ታህሳስ 14 ቀን 2009 ዓ.ም

#1501- 275 Slater St., Ottawa, Ontario, Canada K1P 5H9
Tel: (613) 565-6637 Fax: (613) 565-9175
Web site: www.ethioembassycanada.org
Email: info@ethioembassycanada.org